# <u>ሞትና ሕይወት!</u>

ፍሬ ተተክሎ ይበቅላል፣
ያድጋል፣ አጉጦም ያብባል፣
አምሮበት ያድራል፣ ይወላል፣
ሽታው፣ መዓዛው ያውዳል፣
በሰውም "ግሩም!" ይባላል፣
ጠውልጎ ይደርቃል፣
ይጣላል፣ እሳት ይቃጠላል።

ይገርማል...
ከፍሬ መብቀል ጀምሮ፣
አጊጦ፣ አብቦና፣ አምሮ፣
በፀሓይ ደርቆና አርሮ፣
እስኪጣል ተሸቀንጥሮ፣
ደደቡና አስተዋይ፣ ደንቆሮ፣
መንገዱ፣ አንድ ነው ተፈጥሮ፣
ይነሳል፣ ይወድቃል...

አምሮበት የተንቆጠቆጠው፣
አስቀያሚውም ሆነ ያጌጠው፣
የለበሰውና 'ራቁቱን የወጣው፣
ባለጸጋውና ድኻ፣ የነጣጣው፣
የቆየ ነው፣ ከጥንቱ የመጣው፣
እንደሰማነውና እንዳየነው፣
ፍጻሜውስ ሞትና ሓዘን ነው!

ግን ታድያ...
የዘሩት ደርሶ መታጨዱ፣
የተረገዘው መወለዱ፣
እንደጊዜው ሁሉም መራመዱ፣
ረግቶ የቆመው መንገዳገዱ፣
ሲሞትም መቃብር መውረዱ፣
ከጥንቱ ይኸው አይደል ፍርዱ!
ነው እንጂ እንዲያ...

እንግዲያውስ ብልሓቱ፡
እንደጊዜው፣ እንደሰዓቱ፣
የተፈጥሮ ሂደቱ፣ ስርዓቱ፣
እንደጉሸማው፣ እንዳመታቱ፣
ደስታና ሓዘን ሁለቱ፣
ሲፈራረቁ በየወቅቱ፣
መቀበል ነው ሳያማቱ።

ካልሆነማ. . .
በቅሎ፣ አብቦ፣ ያፈራ፣

ታጭዶ፣ ካልለቀቀ ስፍራ፣
ያምናው ጤጅ ካልለቀቀ እንስራ፣
ካልቆሸሸ፣ ያታጥቦ የጠራ
ጠማቂ፣ አጣቢው ምን ይሥራ?
አዲሱስ ዘር ከምን ላይ ይዘራ?
ለመኸርም አይኖር አዝመራ!
ምድረ - ዓለሙ ሆነ ጠማሚ..

በሰዓቱ ደስታው ጠፏል፣
የኖረውም ሞቶ አብቅቷል፣
ሌቱ አልፎ፣ ፀሐዩም ወጥቷል፣
ሃብታም የነበረው ደኽይቷል፣
ድሃ ወም አልፎለት በልጽጓል፣
የሞተውን ሕያው ተክቶታል፣
ጨልማውን ደምቆ አብርቶታል፤

ወይ ታምር...
መቃብሩም ኖራ ተለቅልቋል፣
ሕያው ነፍስም መሬት አጥለቅልቋል፣
ሕይወትም ሞትን አሸንፏል፣
ግን ሁለቱም ተቆላልፈዋል...
ሞት ከሌለ ሕይወት ወሎ አያድርም፣
ያለ ሕይወት ሞት ፍጹም አይኖርም!
ዕጹብ፣ ወመንክር...

ገ/ኢ.. ጉርፋ።
April 2005